የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10[th] Year No. 53
ADDIS ABABA-15[th] June, 2004


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፰/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ
(ማሻሻያ) አዋጅ.. ገጽ ፪ሺ፮፻፶፰


## CONTENTS


Proclamation No. 408/2004
Addis Ababa City Government Revised charter
(Amendment) Proclamation .... Page 2658


### አዋጅ ቁጥር ፬፻፰/፲፱፻፺፮

### የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ እንደገና እንዲሻሻል ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፰/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ማሻሻያ**

የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል::

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሸ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሸ) ተተክቷል::

"ሸ. የወራሽነት፣ የባልና ሚስትነት፣ የሞግዚትነት እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ:

### PROCLAMATION NO. 408/2004.

### A PROCLAMATION TO AMEND THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REVISED CHARTER PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government Revised Charter (Amendment) Proclamation No. 408/2004."

**2. Amendment**

The Addis Ababa City Government Revised Charter proclamation No. 361/2003 is here by amended as follows.

1/ Sub Article (1) "h" of Article 41 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article 1, 'h'.

"h. application for certificates of succession, marriage and guardianship"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ /ሐ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) ተተክቷል።

"ሐ.በፌዴራል ወንጀሎች ላይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር ፴፫ ፴፭፣ ፶፫፣ ፶፱ መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮቹን መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት"

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፮ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተጨምሯል።

"፲.በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት በመታየት ላይ የነበሩና በአዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ በከተማው ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሥር የማይወድቁ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት መታየታቸው ይቀጥላል"

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2/ Sub-Article (2) "c" of Article 41 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article 2, /c/.

"c. without prejudice to the jurisdiction of federal courts on the substance of federal offenses, cases brought in accordance with Article 33, 35, 53 and 59 of the code of criminal procedure of 1961"

3/ The following new Sub-Article (10) is added under Article 66 of the proclamation:

"10. cases pending before the Addis Ababa Municipal Courts, but do not fall under jurisdiction of the Addis Ababa City Court in accordance with Proclamation 361/2003 shall continue to be adjudicated by the city court."

3. **Effective Date**

This Proclamation shall come in to force as of 15th day of June, 2004

**Done at Addis Ababa, this 15th day of June, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**